# <u>ሙሾ ይረገድለት</u>

ከቀመሩ ደሳለኝ

ኃዘንተኛዋ ሴት ያቺ አሽሙረኛ
አነባችው እንባ አወይ መከረኛ

ሙሾን አወረደች እርር ድብን ብላ
በልብ ሃዘኗ እንድዲያ ተበድላ

ሰው ይሙት አይባል ሁሉ የእግዜር ሥራ
ያ መለስ አስተዋይ የዕውቀት ጎተራ
ድንገት አመለጠ ከደደቢት ጎራ
ቅንድቡ ያማረው ገባ ከሞት ተራ
እንግዲህ በሲኦል ዛሬም እሱ ይምራ

ይቺ አሽሙረኛ አልቅሳ አስለቀሰች
እንባ ሳታወጣ ውሸት እያነባች
በዚያ በቅንድቡ አፈር ሲደፋበት
የወገን ሕመሙን ቁስሉን ነካችበት
ጭንቅና መከራው ስቃዩን ያየበት
ሃዘኑ ጥልቅ ሆነ ተነካ ልባቸው
የሃያ አንድ ዓመት አገንፍሎ ዓይናቸው።

መለዕከ ሞት መጣ ዙሪያውን ሠፈረ
በስፈሩት ቁና መሰፈር ካልቀረ
ባይሞትም ሞቶአል፣ ወገን ካለቀሰ ቆየ ከቀበረ

ዋይ ዋይ ሙሾ ይረገድለት
ዋይ ዋይ ይወገር ደረት
ለዚያ ያደዋ ልጅ ይለቀስለት

ማርገጃ ላይ ሆኜ ደረቴን ስመታ
ተንሰቅስቄ አልቅሼ እድሜዬን በኋይታ
ዘመኔን ቆጠርኩኝ እንቆቅልሽ ሰርታ
ይቺም እንቆቅልሽ ሕልም ሆና ተፈታ
እራሴን አየሁት በኃዘን በድስታ።

ዋይ ዋይ ሙሾ ይወረድለት
ዋይ ዋይ ይለቀስለት

ቢሞት እንጂ መለስ ነገር ነበር ሱሱ
ዝምታን አታውቅም አስችሏት ምላሱ
የምስጥር ወዳጆች ሸሽገው ሞቱን
ደብቀው አቆዩ ዘመድ ሃዘኑን

አልታየ አደባባይ ቀርቦ በሰዎች ፊት
ተደብቆ አልቀረ ተወራ በስፋት

ያርጂ አፉ ሰፍነው የለውም መከደኛ
አገርን የሸጠ ከፋፋይ ከፉኛ
ሕዝብን ያሰቃዬ ጨካኝ ሰው ሴረኛ
ያ መለስ ዜናዊ ከሃዲ- ተንኮለኛ
የምሥራች ሞተ ብሎ ነገረኛ !

ሞቱን መንገርና ማዘን ተሳናችሁ
የዚያን የጀግና ሰው ሞት አራከሳችሁ
የሞተውን መለስ አልሞተም አላችሁ
ሞትእኮ የማይቀር ነው ምን አስጨነቃችሁ
የሰራችሁት ነው አገር የሸጣችሁ ?

ስቲ ዘመድ ይስማ ይለቀስለት
ተጠቃሚ ሁሉ ሙሾ ያውርዱለት
ለዚያ አፈ ጮሌ ሰው ይወገር ደረት
ከዶ ለሚያስከደው መሪ ለውሸት
ዋይ ዋይ ያድዋ ልጅ ይረገድለት
ዋይ ዋይ ይባልለት ይለቀስለት

ኮንትራትህ ገና የአምስት አመት
ሕዝብን ለማሳደድ፣ ለአገር ልማት
ምነው ቃልህን አጠፍህ ተቻኮልህ ለሞት
ለማን አደራ አልከ የገባህውን ቃል
ፈጣሪ ሲያስጠራህ ስትገባ ከሲኦል
ብቻውን አይሄድም የአድዋ ልጅ
ስብሃት፣ በረከት በርከት ይበሉና ይከተሉት እንጅ

ዋይ ዋይ ሙሾ ይረገድልት
ዋይ ዋይ ይባልለት ይለቀስለት
ዋይ ዋይ  ሙሾ ይወረድለት ይለቀስለት።